# በሳን ሆዜ ከተማ በሐገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ከፍተኛ የሐገር ፍቅር እና የትብብር መንፈስ በታየበት ሁኔታ ተጠናቀቀ።

በኢትዮጵያ ያለውን የፖለቲካና ማህበራዊ ቀውስ አስመልክቶ እሁድ ፌብሩዋሪ 14 ቀን፣ 2016 ከቀኑ 2:00pm 7:30 pm በሳን ሆዜ ከተማ ማሶኒክ ሴንተር፤ የተጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ አራት ተናጋሪ እንግዳወች፣ የእምነት አባቶች፣ እንዲሁም ከተለያዩ የሰሜን ካሊፎርኒያ ከተሞች የመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት ሲሆን ከፍተኛ የሐገር ፍቅር ስሜት እና የትብብር መንፈስ በታየበት ሁኔታ ተጠናቋል።

አዘጋጅ ኮሚቴውን ወክለው ስብሰባውን የመሩት ዶ/ር አበበ ገላጋይ፤ የውይይቱ ትኩረት ለሱዳን ስለተሰጠው የሀገራችን ለም መሬት፣ በወገናችን ላይ ስለደረሰው የድርቅና የረሀብ አደጋ፣ ስለሰብአዊ መብቶች መጣስ፡ የህዝብ መፈናቀል እና የኢትዮጵያ ህዝብ የአብሮነት ትስስሮች ላይ መሆኑን ገልጸው፤ አላማውም በተለያዩ ምክንያቶች የተራራቀውን ማህበረሰባችን በማቀራረብ የጋራ ችግሮቹን በጋራ ተወያይቶ የጋራ መፍትሄ ለመሻት መሆኑን ገልጸዋል። በመቀጠልም ስብሰባውን በቡራኬ ለመክፈት በሕዝቡ መሃል የተገኙትን የሐይማኖት አባቶች ወደ መድረኩ ጋብዘዋል። በስበሰባው የተገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እና የእስልምና እምነት አባቶች፤ አንድ ላይ ቆመው፣ ስለተራበው ህዝብ በጋራ በመጸለይ፣ ስብሰባውን በቡራኬ ከፍተዋል። በተጨማሪም፤ ሁለቱ አባቶች ሀገራችን የተከሰተውን የረሀብ አደጋ ለመታደግ ኢትዮጵያውን ሁሉ መርዳት እንደሚገባቸው በማሳሰብ፤ ስብሰብው የተሳካ እንዲሆን ምክራቸውን በአንድ ድምጽ አስተላልፈዋል።




የሀገር ፍቅር ቀስቃሺ መልክቶችን ያስተላለፉት የሀይማኖት አባቶች ብቻ አልነበሩም። ይህ ስብሰባ ተራርቀው የቆዩ የማህበረሰባችን ክፍሎች የተገናኙበት በመሆኑ፣ በአባቶች የተገለጸው የሀገር ፍቅር ቀስቃሽ ምክር በወጣቶች የበለጠ ተንጸባርቆል። ከኦሮሞ እና የአማራ ብሔረሰቦች የተወጣጡ ወጣቶች ያቀረቡት ልዩ ልዩ ባህላዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ፤ ስብሰባውን ደማቅ አድርጎታል። የውይይቱን ሰፋ ያለ ጊዜ የወሰደው፤ የአራቱ እንግዶች ገለጻና ውይይት ሲሆን፤ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ለንጂሶ በመሬት፣ ህዝብና መንግስት፤ ኢንጂነር ፍስሐ አጥላው፣ ስለድርቅና ረሀብ፤ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ፣ ስለኢትዮጵያውያን የአብሮነት ትስስሮች አቶ ሊቁ እጄጉ ለሱዳን ሊሰጥ ስለታሰበው የኢትዮጵያ መሬት ሰፊ ገለጻና ውይይት አድርገዋል።



የኢትዮጵያ ደንበር ጉዳይ ኮሚቴና አባል የሆኑት አቶ ሊቁ እጅጉ፤ ሕወሀት ለሱዳን እሰጣለሁ የሚለው መሬት፤ የኢትዮጵያ ሀብት መሆኑንና አርሶ አደሩ ለብዙ ዘመናት ተከላክሎ ያቆየው ሀብቱ መሆኑን ገልጸው፤ እንግሊዞች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ኢትዮጵያውያን ሳይገኙበት የከለሉት ካርታ፤ ከአጼ ምኒልክ ጀምሮ ማንም መንግስት ያልተቀበለው መሆኑን ገልጸዋል። ቀጥለውም፤ ሕወሀት የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን አሳልፎ መሸጥ የመረጠው፤ የያዘውን ዘረኛ አገዛዝ ለማራመድና እስከ ጋምቤላ ድረስ ታላቋን ትግራይ ለማስፋት ያለውን ህልም ለማሳካት የታቀደ የረጅም ጊዜ ፕላን መሆኑ ገልጸዋል። በመጨረሻም፤ ኢትዮጵያውያን ህብረታችንን በማጠንከር፣ ያለውን ስርአት ካልቀየርን፤ የሕወሀት መሪዎች መሬታችን ለሱዳን ከመስጠት እንደማይመለሱ ጠቁመዋል።ወያኔ



በአሁኑ ወቅት የሀገራችን መሬት ለሱዳን መስጠት የወሰነው፣ የተቃዋሚ ሀይሎቸ ከጐረቤት ሃገሮች ድጋፍ እንዳያገኙ ለእጅ መንሻነት ሲሆን በዚህም ጸረ ኢትዮጵያ ተግባሩ እንደነ አጠናው ዋሴ ያሉ፣ ብዙ ሀገር ወዳድ ዜጎች ህይወታቸውን እንዳጡ አስረድተዋል።

ቀጥለው የተናገሩት ተጋባዥ እንግዳ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ፤ በዚህ ስብሰባ ያተኮሩት፣ ኢትዮጵያውያንን በታሪክ፣



በባህል፣ እና በደም የሚያስተሳስሩን የጋራ ዝምድናዎች ላይ ነበር። ዶ/ር ፍቅሬ በደም የሚያስተሳስሩን የጋራ ዝምድናዎች እያሉን፣ በልዩነታችን ላይ ማተኮራችን ችግሮችን የሚያባብሱ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ወደፊትም ማደግ እና መበልጸግ የምንችለው በሚያቀራርቡን እና በሚያስተሳስሩን የጋራ ዝምድናዎች ላይ ስናተኩር ብቻ እንድሆነ አስገንዝበዋል። ቀጥለውም ታላላቆቹ የአውሮፓ ሀገሮች እነፈረንሳይ እና ጀርመን ደንበራቸውን እያፈረሱ በሚተባበሩበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለብዙ ሺህ ዘመናት በባህል በጋብቻ በታሪክ ተሳሰረን የኖርን ኢትዮጵያውያን መለያየት እና ማጋጨት ለዲሞክራሲ ግንባታም ይሁን ለወደፊቱ ሰላም የማይበጅ መሆኑን ጠቁመው፤ ወደ ታሪካችን ተመልሰን ወዳጅነታችንና ፍቅራችንን ልናድስ እንደሚገባን አሳሰበዋል።

ሌላው ተናጋሪ፣ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ለንጅሶ፤ የመሬት ይዞታ በሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በተለይም በኦሮሞ ማህበረሰብ ላይ ኢኮኖምያዊ ብቻ ሳይሆን፣ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ስነልቦናዊ ቁርኝት ያለው መሆኑን አብራርተው፣ ህዝብን መሬት አልባ ማድረግ፤ እምነቱን፣ ባድማውን፣ ሀብቱንና ማህበረሰቡን፣ ባጠቃላይ ማንነቱን እንዲያጣ የሚያደርግ መሆኑን ገልጸዋል። ቀጥለውም፤ ገዥዎች በስልጣን ለመቆየት መሬት ዋና መሰረታቸው በመሆኑ፤ በኢትዮጵያ ያለው የመሬት ይዞታ ከወያኔ ህገ መንግስት ጋር የተቆራኘ መሆኑን፡ ይህም ሂደት መሬት ተረካቢው ወደ ገዥነት፤ መሬት ተነጣቂውን ደግሞ፤ ወደ ተገዥነት የሚያሸጋግር መሆኑን አስረድተው መንግስት የያዛቸውን የጋምቤላ፣ የኦሮሞ፣ የጎንደር (ወልቃይት) መሬቶች ከለቀቀ በስልጣን እንደማይሰነብት ስለሚያውቅ በቀላሉ ፖሊሲውን ሊቀይር እንደማይችል በማስገንዘብ፡ የህዝቡ ምርጫ፤ አሁን እንደሚታየው ቆርጦ ለመብቱ መታገል ብቻ እንደሚሆን አብራርተዋል።



የስብሰባው የመጨረሻ ተናጋሪ እንግዳ ኢንጂኔር ፍስሐ አጥላው፤ በኢትዮጵያ ስላለው ድርቅና ረሀብ ጉዳይ ሰፋ ያለ



መግለጫ አቅርበዋ። ኢንጂኔር ፍስሐ በአሁኑ ወቅት በሀገራች የተራበው ህዝብ ቁጥር ከ10 ሚሊዮን በላይ መሆኑን አሳስበው፤ ረሀቡ ለፖለቲካ መጠቀሚያ እንዳይሆን እና ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወገኖቹን ለመርዳት የሚችለውን ሁሉ እንዲያደርግ ተማጽነዋል። በመጨረሻውም፤ የሎሬት ጸጋየ ገብረመድህንን እና አንድ የራሳቸውን ግጥም በማንበብ እጅግ ቀስቃሽ መደምደሚያ አቅርበው ወገኖቻችን እንድናሰብ ጥሪ አድርገዋል።

ከአራቱ እንግዶች ገለጻና ውይይት፤ ቀጥሎ፤ የጥያቄና መልስ ዝግጅት ቀርቦል። የተለያዩ የማህበረሰብ እና የሐይማኖት መሪዎች በሕዝቡ መካከል መኖር ስለሚገባው አንድነት አጽንኦት የሰጡ ነበሩ። በርካታ የስብሰባው ተሳታፊወች ጅምሩ አዲስ ምእራፍ ሊከፍት የሚችል መሆኑን ገልጸው፣ ባለመተባበራችን ጥቂት ወያኔዎች አብዛኛውን ህዝባችን ላይ ግፍና በደል እየፈጸሙ መሆናቸውን አስረደተው ወደፊትም ተራርቆ የቆየውን ማህበረሰባችን በማቀራረብ አንድነታችን አጠንክረን ሀገር ውስጥ ለዲሞክራሲ እና ለለውጥ ለሚታገሉ ሀይሎች አጋር መሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

በተጨማሪም፤ በሀገራችን የተከሰተው የመሬት ዘረፋና የህዝብ መፈናቀል እና የሰብአዊ መብት ጥሰት ያሳሰባቸው በርካታ የስብሰባው ተሳታፊዎች ባቀረቡት ሀሳብ መሰረት በሰሜን ካሊፎርኒያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሀገር ቤት በህዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል ለአለም በማጋለጥ እና ሁለገብ ድጋፍ በማድረግ ከወገኑ ጎን መሰለፍ እንዳለበት የጋራ ስምምነት ተደርሶኣል። ይህንንም ጉዳይ አጥንቶ የሚያቀርብ አራት የተለያይ የጥናት ቡድን ሰይመዋል።

የስብሰባው የውይይት መንፈስ እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል

1. ሕወሐት ኢሕ አዴግ፤ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያካሂደውን ኢሰብአዊ ግፍና በደል በጥብቅ አውግዟል፤

2. ለነጻነትና ፍትህ ድምጻቸው ያሰሙ ወገኖቻችን ያለ ፍርድ የተገደሉ፣ የቆሰሉ፣ የታሰሩና የተሰደዱ ወጎኖቻችንን ጎን በጋራ የምንቆም መሆናችንን እያረጋገጥን፣ በህዝብ ላይ ወንጀል የፈጸሙ ባስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ ጠይቋል።

3. ወገኖቻችንን ከመሬታቸው እያፈናቀሉ፤ መሬት የሚዘርፉ የወያኔ ባልስልጣኖች፣ የውስጥና የውጭ ሀይሎች፣ ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ አስጠንቅቋል፤

4. ወያኔ ኢሕአዴግ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በደም ያቆየውን ዳር ደንበር ቆርሶ ለሱዳን ለመሸጥ የጀመረውን የሀገር ክህደት ተግባር በጥብቅ በማውገዝ፤ የኢትዮጵያ ጦር ሀይሎች እና ጀግናው ህዝብ እንደ ጥንቱ ተባብሮ ደንበሩን እንዲያስከብር አሳስቧል፤

5. የኢትዮጵያና የሱዳን መንግስታት በሀገራችን ላይ የጀመሩት ሴራ በማጋለጥ፤ ለተባበሩት መንግስታት በድንበር ኮሚቴ የገባውን ደብዳቤና ፊርማ ከልብ የምንደግፍ መሆናችን እየገለጽን፤ የአሜሪካን ባለስልጣኖችን በችግሮቹ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ጥረት እንዲደረግ ጠይቋል።

6. በኢትዮጵያ የደረሰው ድርቅና ረሀብ ህዝባችን ለደረበት አደጋ ቀድመን መገኘት ስላለበን ገዥው ፓርቲና አደጋውን ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ጠይቋል፤

7. በተጨማሪም በዛሬው እለት በሳንሆዜ ከተማ የታየው የሃገር ፍቅር ስሜት በሌሎች ከተሞችም እንዲስፋፋና ወገን ለገወገኑ እንዲደርስለት ጥሪ በማድረግ እና፤

8. በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ጠንካራ ማእከሎችን በመፍጠር እንድንረዳዳ ጥሪ አድርጓል፤

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!

ድል ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ!!!

ለበለጠ መረጃ
ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን
Concerned Ethiopians
Email: Concernedethio@gmail.com
408-482-6497 or 408-499-4116